# ዶክተር ዜሮ

ልደቱ በጋሻው የኛው ድ/ር ዜሮ
እያደሩ ጥጃ ከንቱ ተመክሮ
አወይ አለመማር ወይ አለመታደል
ስንቴ ሰው ይሞታል እየገባ ገደል?

ማስተዋል ለሚችል አርቆ ለማየት
ዕድሜዬም ትምህርት ነው እንደ ቀለም እውቀት
ለዶ/ር ዜሮ ግን የኮነግ አብነት
አልታይህ ያለው የመገንጠል ዕምነት
እንደ ብርሃኑ የፈረንጅ ቅጥረኛ
እንዳይሆን ጠርጥሩ የጀሮ ቀበኛ!

............

ሳቂ ወይም አልቅሽ
እንዳትስቂ ደስታ የነሳሽን ህዘን
መለኪያ ፈልገሽ በህሊናሽ ማዕዘን
መሆንሽን አውቀሽ የሙት ባልደረባ
ልሳቅ ታልሽ ሳቂ ወይ ታጠቢ በዕምባ።

ህዘንተኛ ሆነሽ የሞተ - በቁሙ
ተልከስክሶ እሚታይ ሰውነትሽ አፅሙ
እያለሽ የሌለሽ ሰው ሆነሽልና
ሳቂ ወይም አልቅሽ በህዝብሽ ገመና።

አገር በቀል ጠላት የውጭ ሰው ጠርቶ
መቆሚያ መሄጃ መራመጃ ነስቶ
መሬቱ አይደለም ወይ ያስወገደሽ ትፍቶ?

ስለዚህ እህቴ ልጆሽን ስትደሪ

ለማጫ ያሰብሽው የመሬት ዕዳሪ

ይታደልሽ እንደሁ ተስፋሽን ሰንቀሽ

ለጌታ አደረና አንቺም እንደ ህዝብሽ

ሳቂ እንደማሽላ እያረረ ውስጥሽ ! !

ሰኔ 2003

ለለምለም ፀጋው ግጥም መልስ

አብርሃም በየነ